

# የተደፈነ ቲዩበርኩይሎሲስ

## Latent Tuberculosis

(Amharic)

## ቲዩበርኩይሎሲስ (ቲቢ) ምንድነው?

ቲቢ አብዛኛውን ጊዜ ሳንባን የሚጎዳ በሽታ ነው፡፡ ቲቢ ሌሎችንም የሰውነት ክፍሎች አጥንቶችንና አንጎልንም ሊጎዳ ይችላል፡፡ ቲቢ የሚይዘው በጀርም ነው፡፡ በሳምባው ውስጥ ቲቢ ያለበት ሰው ሲስል ወይም ሲያስነጥስ ጀርሞቹ ወደ አየር ይተላለፋሉ፡፡ ጀርሞቹ ሳንባን ወይም ሌላ የሰውነት አካል በመጉ ዳት አንድን ሰው በጣም ሕመምተኛ ያደርጋሉ፡፡ ይህም የቲቢ በሽታ ይባላል፡፡

የቲቢ በሽታ በመድሐኒት ሊድን ይችላል፡፡

## የተደፈነ ቲቢ ምንድን ነው?

የተደፈነ ቲቢ ከቲቢ በሽታ የተለየ ነው፡፡

የተደፈነ ቲቢ ያለው ሰው ውስጥ የቲቢ ጀርሞቹ የተኙ ናቸው፡፡ ጀርሞቹ እስከተኙ ድረስ ስውየው በጥሩ ጤንነት ላይ ይገኛል፡፡ የተደፈነ ቲቢ ያላቸው ሰዎች በሽተኛ አይደሉም፡፡ የቲቢ ጀርሞችን ወደ ሌሎች አያስተላልፉም፡፡

## የተዳፈነ ቲቢ ምልክቶች ምንድን ናቸው?

የህመም ምልክቶች የሉም፡፡ የቆዳ ምርመራ ቲቢ እንዳለብህ ሊነግርህ ይችላል

ቲቢ ያለባቸው ሰዋች ህመምተኛ አይደሉም፡፡



*የተዳፈነ ቲቢ ያለባቸው ሰች ደህና ናቸው፡፡*

*የቲቢ ጀርም ወደ ሌላ ሰው አያስተላልፍም፡፡*

## በሽተኛ ካልሆንኩ ለተደፈነ ቲቢ መታከም ለምን ያስፈልገኛል?

አንዳንዴ ጀርሞቹ ከወራትና ከዓመታት ምኝታ መንቃት ይችላሉ። ጀርሞቹ በሳምባ ወይም በሌላ የስውነት ክፍል ላይ የቲቢ በሽታ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።



*የቲቢ በሽታ ከያዘህ በጣም ልትታመም ትችላለህ እና ጀርሙን ለቤተሰቦችህ በሌሎች ላይ ማስተላለፍ ትችላለህ።*

የተደፈነ ቲቢ ያለባቸው ሕፃናት በቲቢ በሽታ ለመያዝ የበለጠ አጋጣሚ አላቸው።

የተደፈነ ቲቢ ካለብህ ዶክተር የተኙትን ጀርሞች ለመግደል ሕክምና እንድታደርግ ይመክርህ ይሆናል። ምንም እንኳን ደህንነት ቢሰማህና ጤናማ ብትሆን ቲቢ እንዳታዳብር እርግጠኛ ለመሆን ሕክምና እንድትወስድ ትመከር ይሆናል።

ሐኪምህ ምን አይነት ሕክምና መውሰድ እንዳለብህ ከአንተ ጋር ይወያያል።

## ለተደፈነ ቲቢ ሕክምናው ምንድን ነው?

የተዳፈነ ቲቢ ሕክምና አብዛኛውን ግዜ በሰውየው ዕድሜና ሌሎች የጤና ችግሮች ላይ ይወስኑታል

ሕፃናት በሕፃናት ሐኪም (ፒዳትሪሻያን) ይመረመራሉ። ፒዳትሪሻያኑ ለሕፃኑ ጥሩ ሕክምና ይገምታል።

ጎልማሶች በተዳፈነ ቲቢ 'ስፔሻላይዝ' ባደረገ ዶክተር ይታያሉ። ዶክተሩ ጥሩ የሆነውን ሕክምና ይገምታል።

ዶክተሩ መድሐኒት ሊሰጥህ ይችላል መድሐኒቱን ለበርካታ ወራቶች መውሰድ ይኖርበታል። የሕክምናው ጊዜ ርዝማኔ የሚወሰነው በመዲሐኒቱ አይነት ነው። በዚን ወቅት ዶክተር ወይም ነርስ በየወሩ ያዩሃል። ምንም እንኳ ጤንነት ቢሰማህም መድሐኒትህን በየቀኑ ወይም ዶክተሩ ባለው መሰረት መውሰድ አለብህ።

መድሐኒትን በተከታታይ ካልወሰድክ የተኛውን ጀርም ላይገለው ይችላል።

ዶክተሩ መድሐኒት ካልሰጠህ ዶክተሩ ወይም ነርሷ ስለ ቲቢ በሽታ ቅድመ ምልክቶች ይነግሩሃል። ከነኚህ ምልክቶች አንዱን ለወደፊት ካየህ ሐኪምህን ወይም ነርስ ሳትዘገይ እይ።

## የትኞቹ መድሐኒቶች ናቸው ጥቅም ላይ የዋሉት?



አይሰናይዚድ (Isoniazid) ወይም (INH) አይ ኤን ኤች አብዛኛውን ጊዜ ለተዳፈነ ቲቢ የሚሰጥ መድሐኒት ነው። የሆነሆኖ አንዳንዴ ሌሎች መድሐኒቶች ሊሰጡ ይችላሉ። መድሐኒቱ በሰውነት ውስጥ የተኙትን ጀርሞች ይገላል።

አይ ኤን ኤች ከ6 እስከ 9 ወራት በየቀኑ መወሰድ ይኖርበታል። መድሐኒቱን ሆድህ ባዶ ሲሆን ውሰድ፤ ለምሳሌ፡

- በየጠዋቱ ከቁርስ አንድ ሰዓት በፊት

ወይንም

- ሁለት ሰዓት ክእራት በኋላ ማታ።

ሐኪምህ (pyridoxine) ፓይሪዶክሲን (ቪታሚን) ሊሰጥህ ይችላል። ይህ መድሐኒት አይ ኤን ኤች በመውሰድ በጎልማሶች ላይ የሚመጡትን ጉዳቶች ለመከላከል ይረዳል።

*ስለተዳፈነ ቲቢ ከተጨነቅህ ስለሕክምና ወይ ተጓደኝ የሆነ ጉዳት ካሰብክ ከዶክተርህ ውይም ከነርስህ ጋር ተነጋገር።*

## የአይ ኤን ኤች (INH) ጉዳቶች ምንድን ናቸው?

አይ ኤን ኤች (INH) አንዳንድ ግዜ በጎልማሶች ጉዳት ሊኖረው ይችላል። በሕፃናት ላይ ጉዳቶች በጣም አልተለመደም።

- ማቅለሽለሽ ፥ ማስታወክ ፥ የሆድ ቁርጠት
- የቆዳ መንደባደብ ወይም ማሳከክ
- በእግርና በእጅ ላይ መደንዘዝ
- ሄፓታየተስ (የጉበት መመረዝ) የሄፓታይተስ ምልክቶች የቆዳ ቢጫ መሆን የአይን ነጭ ክፍል ቢጫ መሆን እና የሽንት መጥቆር ናቸው።

ጉበትህ ጤነኛ መሆኑን ለማወቅ ሐኪምህና ነርስህ ደምህ በተከታታይ ይመረምራሉ

ሌላ ጉዳት ካየህ መድሐኒቱን መውሰድ አቁምና ወዲያውኑ ለሐኪምህ ወይም ለነርስ ስልክ ደውል።





# የተዳፈነ ቲቢ ካለብህ የሚከተሉትን አስተውል፡....

- የቲቢ በሽታ የለብህም
- ጀርሙን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አትችላም
- ጤንነት ቢሰማህም ሕክምናውን መቀጠል አለብህ

የበለጠ መረጃ ከፈለግህ ወይም ከዶክተርህወይም ከነርስህ ጋር መነጋገር ከፈለግህ፡

*( TB doctor / nurse details here)*

MINISTRY OF HEALTH
MANATŪ HAUORA
Ministry of Health, June 2003. Code: 1435 AMH